# ዜና መጽሔት

ቅጽ 2 ቁጥር 4 መጋቢት 2013 ዓ.ም





**ትምህርታዊ ጉብኝት በሀረር**

መጋቢት 30/2013 ዓ.ም

ትምህርታዊ ጉብኝት በሀረር ከተማ ተደረገ፡፡
ሀረር ከተማ ከተቆረቆረች 1,000 ዓመት በላይ የሆናት ከቀደምት የአገራችን ከተሞች አንዷ ከመሆኗ ባሻገር ለቱሩዝም ሳቢ በመሆኗ የቱሪዝም ተማሪዎች እንዲጎቦኙ ተደርጓል፡፡
የሁለተኛ ዓመት የቱሪዝም ሰልጣኞች በዚህች ከተማ የሚገኙ የባህልና ቅርስ ሀብቶችን እንዲሁም በቱሪስት የሚጎበኙ ስፍራዎችን ያስጎበኙት የከተማው የቱር ጋይድ ባለሙያ አቶ አዮብ አምዴ ሲሆኑ ከከተማው አመሠራረት ጀምሮ ስለጀጎል ግንብና ስለአምስቱ የጀጎል በሮች ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡
አምስቱ የጀጎል በሮች ሸዋ በር፣አርጎባ በር፣ሄሬር በር፣ ሰንጋ በር እና በድሬ በር ስሆኑ በግንቡ ውስጥ 99 መስግዶችና አንድ ቤተክርስቲያን እንዳለም አስጎብኚው ተናግሯል፡፡
360 ጠባብ መንገዶችና አንድ አስታራቂ መንገድም በውስጡ እንዳለበት በመግለጽ በከተማው ሁለት የመንግስት እና አንድ የግል ሙዚዬም ያለ ሲሆን በውስጥ ያሉ ቅርሶችና ስለጥንታዊ የሀረር ቤቶች አሰራር ሰፊ ማብራሪያ አስጎብኚው ሰጥተዋል።
በተጨማሪም ከተማዋ የምትታወቅበትን የጅብ መመገብና ጅብን እንዴት ማላመድ እንደቻሉ ለሰልጣኞቻችን ገለፃ ተደርጎላቸዋል።



## በኮምኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

## የተግባር ስልጠና በሐረማያ ሀይቅና በባቢሌ ከተማ

መጋቢት 29/2013 ዓ.ም




የሁለተኛ ዓመት የቱሪዝም ትምህርት ክፍል ሰልጣኞች ስለ ሐረማያ ሀይቅና በባቢሌ ስለሚገኙ የቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች ስልጠና ተሰጣቸው።

ስልጠናውን የሰጡት የቱሪዝም ትምህርት ክፍል መምህር ማሩ እማኙ እንደተናገሩት የሐረማያ ሀይቅ ከአሥር ዓመት በፊት የደረቀ እንደነበርና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ተፈጥሯዊ እንክብካቤ ተደርጎለት ሐይቁ መልሶ ማገገም መቻሉን አስረድተዋል፡፡


በሀገራችን በሁሉም አከባቢዎች ችግኝ የመትከል መርሃ ግብር ተግባራዊ መደረጉ ደርቀው የነበሩ የውሃ አካላት ዳግም መምጣታቸው አንዱ በጎ ማሳያ መሆኑን በሐሮማያ ሐይቅ የታየው እውነታ ምስክር ነው ብለዋል፡፡ በመሆኑም በሐይቁ ላይ ኑሯቸውን ያደረጉ አዕዋፋትና እና ሌሎች የውሃ አካላትን ማብራሪያ አድርገዋል።

ባቢሌ ከተማ ከሀረር በ40 ኪሎ ሜትር የምትገኝ ሲሆን ከከተማው በአራት ኪሎ ሜትር ርቀት በእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ምክንያት የተፈጠሩ የተለያዩ የድንጋይ ቅርጾች የሚታዩበት ልዩ ስሙ ደኮታ ስለተባለው ቦታም ሰፊ ማብራሪያ በመምህር ማሩ ተሰጥተዋል።

በተጨማሪም የግመል ገበያ የሚደረግበትን ቦታ በማየትና በአካባቢው ስለሚገኙ ዕጽዋት ገለጻ ተደርጓል፡፡















## ድሬዳዋ

ድሬዳዋ ከተማ አመሰራረቱ ከባቡር ጋር የተያዘ ሲሆን የመጀመሪያው በፕላን የተሰራ ከተማ እንደሆነም ይነገራል፡፡ የንግድ እና ስፖርት ማዕከል እንዲሁም የመቻቻል መግባባት ፤እንግዳ ተቀባይነት ተምሳሌት፣ ልሳነ-ብዙህነትና corrupted language, የቤት አሰራር (architectural diversity)፣የውጭ ዜጎች ስያሜ ያላቸው ታሪካዊ ሰፈሮች (quarter) ፤የተለያዩ ምግቦች(Gastronomy) ፤ሀይማኖቶች (religious diversity ) አሏት፡፡
ከተማዋ የተለያዩ ሰፈሮች ያሉዋት ሲሆን ከነዚህም መካከል መጋላና ከዚራ የሚባሉት ቀዳሚዎች ናቸው፡፡ መጋላም ገና ከምስረታዋ በተለያዩ ንግዶች ላይ የተሰማሩ የአረብና የህንድ ነጋዴዎች መኖሪያ ነች። በሂደትም ደማቅ የንግድ ማዕከል ለመሆን በቃች ። ጠባባብ መንገዶቿና የአረቦች አሻራ በስፋት የሚስተዋልባቸው ሱቆችና መኖሪያ ቤቶቿ የመጋላ ልዩ መገለጫዎች ናቸው። የባቡር መስመር ግንባታውን ተከትሎ በተፈጠረው የስራ እድል ተጠቃሚ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ደግሞ ከደቻቱ ወንዝ በስተቀኝ ባለው ቦታ ላይ የሰፈሩ ናቸው።

ከዚራ ማለት በአረቢኛው በውሃ የተከበበ ቦታ ማለት እንደሆነ ተገልጸዋል፡፡ ከዚራ (በፈንሳይ ፕላን የተሰራ የግሪክ፤የአርመን፡ የኢጣልያን) እና መጋላ ሰፈሮችን ጭምሮ አንደኛ አዲስ ከተማ፣ ግሪክ ካምፕ(በጣሊያን ማስተር ፕላን የተሰራ ሙሉ የነሱን አሻራ የያዘ ሰፈር )፣ ገንደ ቆሬ፣ ዲፖ፣ ሳቢያን፣ ለገሀሬ ፣ ኮኔል፣ አፈተ ኢሳ፣ ቀፊራ፣እና የመሳሰሉት የድሬዳዋ ሰፈሮቸ የቱሪስትን ቀልብ ይስባሉ። ሰልጣኞቻችን እነዚህን ሰፈሮች በአካል ጎብኝተዋል፡፡



በአጠቃለይ በድሬዳዋ ከተማ የሁለተኛ አመት የቱሪዝም ማኔጅመንትና የቱሪዝም ማርኬትግ ሰልጣኞች በ1902 ዓ.ም የተጀመረውን የባቡር ጣቢያ አመሰራረቱንና አሁን ያለበትን ሁኔታ ጎብኝተዋል፡፡ በተጨማሪም የድሬዳዋ ሚሊኒየም ፓርክ በመጎብኘትና በውስጡ የሚገኙ የተለያዩ የብሔር ብሔረሰብ ቤቶችን ተመልክተዋል፡፡
ሰልጣኞች በድሬዳዋ ከተማ ያገኙትን ዕውቀት እርስበርስ በመወያየትና በማዳበር ጊዚያቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ተደርጓል፡፡









## የተማሪ ተወካዮች በመማር ማስተማር ዙሪያ በጥንካሬና በድክመት የሚነሱ ጉዳዮች ላይ ተወያዩ

መጋቢት 24/2013 ዓ.ም

የማሰልጠኛ ማዕከሉ የበላይ አመራሮችና የተማሪ ተወካዮች በመማር ማስተማር ዙሪያ በጥንካሬና በድክመት የሚነሱ ጉዳዮች ላይ ተወያዩ።
በውይይቱ ሁሉም የተቋሙ የበላይ አመራር በተገኙበት የተማሪ ተወካዮች በተቋሙ የሚታዩ ጠንካራና ደካማ ጎን በማንሳት በቀጣይ ለመማር ማስተማር ሂደት ይረዳን ዘንድ በነጻነት እንዲያቀርቡ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት በማሳሰብ ውይይቱን አስጀምረዋል፡፡
በማሳሰቢያው መሰረት የተማሪ ተወካዮች በተቋሙ የሚታዩ ጠንካራ ጎኖች የበላይ አመራር አካላት የተማሪውን ጥያቄዎች ወደታች እየወረዳችሁ በማየት ለመፍታት የሚደረገው ጥረት ጥሩ እንደሆነና በተቋሙ የሚሰጡ ትምህርቶችን በተክኖሎጂ መጠቀሙ የሚበረታታ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡
ተወካዮቹ በድክመት ያነሷቸው በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተዘጋጅተው የሚያስተምሩ መምህራን እንዳሉ ሁሉ ያለዝግጅት መግባትና የሚቀሩ እንዳሉ ይህንንም የበላ አመራሩ ቁጥጥር እንዲያደርጉበት ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡
በተጨማሪም ተወካዮቹ ለቀጣይ የሚጠቅሙን ነገሮች ላይ ትኩረት በማድረግ የሚገቡ ናቸው ያሏቸውን ለቋንቋ ትምህርት ቱኩረት ቢሰጥ፣ የኢንተርኔት አገልግሎት ግቢ ውስጥ ሙሉ ቢሆን፣ ቤተመጸሐፍት ቅዳሜና እሁድ ቢሰራ፣ የመማሪያ ክፍል አደረጃጀቶች ችግር ቢፈታ፣ የውጤት አሰጣጥ ከሬጅስትራር ጋር የተያያዙ ችግሮች መፍትሔ ቢያገኙ፣ የግቢ ጽዳትና የውሃ ችግር ቢስተካከል እንዲሁም መልካም ተሞክሮዎች ቢበረታቱ የሚሉ በርካታ ጉዳዮችን አንስተዋል፡፡
በሌላም የኪስ ገንዘብ አነስተኛ በመሆኑ ለብዙ ችግር መጋለጣቸውንና ለኮቪድ መከላከያ የሚሰጡ እንደማክስና ሳንታይዘር ያሉት በጊዜ ቢቀርብልን በማለት ሃሳባቸውን ገልጸዋል፡፡
የተቋሙ አካዳሚክና ምርምር ዲን አቶ አብርሃም ለገሰ እና የአስተዳደር ልማት ዲን አቶ ዳንኤል በቀለ ከተማሪዎች በዘርፋቸው ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል፡፡
የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ተማሪ ተወካዮቹ በጠናካራና በደካማ ጎን የቀረበውን ሀሳብ አመስግነው፤ በተቋም ደረጃ ሊስተካከሉ የሚችሉ የኮቪድ ፕሮቶኮል እቃዎች በቶሎ እንዲደርስ ለማድረግና በቅጥር ግቢ ውስጥ የኢንተርኔት አክሰስ ሙሉ እንዲሆን እንዲሁም የዓመታዊ ሁነት ስራው ከመማር ማስተማር ሂደቱ ጋር ተቀናጅቶ ዘመናዊ በማድረግ እንደሚሰሩ ተናግረዋል፡፡
ዋና ዳይሬክተሯ የተማሪዎች የኪስ ገንዘብ በተቋም ደረጃ ማስተካከል ባይቻልም የማደሪያ ጉዳይ ቀጣይ እቅዳችን አድርገን እንሰራለን በማለት ውይይቱን አጠናቀዋል፡፡











# የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል የ6ወር ሥራ አፈጻጸምና የባለድርሻ አካላት ውይይት ተካሄደ፡፡

መጋቢት 11/2013 ዓ.ም

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል የ6ወር ሥራ አፈጻጸምና የባለድርሻ አካላት ወይይት መድረክ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሴቶች ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ም/ኃላፊዎች ከዘርፉ ጋር የሚሰሩ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ተካሂዷል፡፡

በውይይቱ መክፈቻ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት እንደገለጹት ተቋሙ በ6ወር ያከናወናቸውን ሥራዎች ለማስቀጠልና ሌሎች የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን ከባለድርሻ አካላትና ተቋሙን በቅርበት ከሚከታተለው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማህበራዊ ዘርፍ ቋሚ ኮሚቴ ጋር መወያየት አስፈላጊ በመሆኑ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

በየጊዜው ተቋሙ የሚያከናውናቸውን ተግባራት መገምገሙ በዘርፉ ብቃት ያላቸውን ሰልጣኞች ለማፍራት የሚያግዝ መሆኑን የገለጹት ወ/ሮ አስቴር የውይይት መድረኩ በተለይም የተቋሙን ደምብ ለማሻሻል ለሚደረገው ጥረት በዚህ መድረክ የተገኛችሁ የስራ ኃላፊዎች የምትሰጡት ሃሳብ በጣም ወሳኝ ነው ብለዋል፡፡

የተቋሙን የ6 ወር ዕቅድ አፈጻጸም የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ በዝርዝር ለተሳታፊዎች አቅርበዋል፡፡

ከቀረበው የ6 ወር የአፈጻጸም ሪፖርት በመነሳት ተሳታፊዎቹ እንደገለጹት የ6ወር አፈጻጸሙ ኮቪድ 19 ወረርሽኝ ዘርፉን በጎዳበት ወቅት ቢሆንም ተቋሙ እንደ አገር የሆስፒታሊቲ ኢንደስትሪው ከመዘጋት የታደገ መሆኑንና በርካታ ስራዎች የተሰሩ መሆናቸውን እንደተረዱ ገልጸዋል፡፡

የተቋሙ ደምብ ማሻሽያና ከመዋቅር ጋር የሚነሱ ችግሮች እንዲፈቱ ሁሉም ባለድርሻ አካላትና የቋሚ ኮሚቴ አባላት ኃላፊነታቸውን እንደሚወጡ እና ወደ ሚመለከተው አካል እንደሚያደርሱም ቃል ገብተዋል፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ የትብብር ስልጠና ማዕቀፍ ሰነድ በተቋሙ አስተዳደርና ልማት ዲን አቶ ዳንኤል በቀለ ለውይይት ቀርቦ የማዳበሪያ ሃሳብ ከተሳታፊዎች ተሰጥቶበታል፡፡









**ስልጠና ተሰጠ፡፡**

መጋቢት 05/2013 ዓ.ም

በሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ከግዥ ጋር በተያያዙ ኮሚቴዎች ላይ ተመድበው ለሚሰሩ ባለሙያዎችና የማኔጅመንት አባላት በግዥ መመሪያዎችና አሰራሮች ዙሪያ የሁለት ቀን ስልጠና ተሰጠ፡፡
ስልጠናው በማሰልጠኛ ማዕከሉ ውስጥ የሚታየውን የግዥ መስተጓጓል ችግሮችን ለመፍታት በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ግዥን ለማከናወን የሚያስችል መሆኑን የፋይናንስና ግዥ አስተዳደር ዳይሬክተር አቶ ዘሚካኤል ጣዕምያለው ገልጸዋል፡፡
በግዥ መመሪያዎችና አሰራሮች ዙሪያ የግንዛቤ ስልጠና መሰጠቱ ግዥ ኮሚቴዎች ላይ ተመድበው ለሚሰሩ የግዥ ሂደትን አውቆ ለመስራት እንደሚያስችል የስልጠናው ተሳታፊዎች ገልጸዋል፡፡
በስልጠናው ላይ መልዕክት ያስተላለፉት የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ አስቴር ዳዊት የግዥ አጽዳቂና ቴክኒካል ኮሚቴዎች በአግባቡ ሰልጥኖ ተቋሙን ከብክነትና ተጠያቂነት መጠበቅ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡